ኢትዮጵያችን

ሰኔ 26 ቀን 2015 ዓ.ም.

# በአማራው ተጋድሎ ድሉ የኢትዮጵያችን ይሆናል

*ጋዜጣዊ መግለጫ ከኢትዮጵያችን ሀገር ወዳድ ወገኖች*

***"መነሻችን አማራ መዳረሻችን ኢትዮጵያ"*** በሚል በቅርቡ እራሱን ይፋ ያደረገው ***"የአማራ ሕዝባዊ ግንባር"*** ሊደገፍና ሊበረታታ የሚገባው ነው። ኢትዮጵያችንን አደገኛ የመበታተን ሁኔታ ውስጥ ሊዘፍቅ የተነሳው በዐብይ አሕመድ የሚመራው ዘረኛ የኦሮሙማ አገዛዝ ሃይ ባይ በማጣቱ አማራው ለራሱና ለሀገሪቷ እልውና እየተፋለመና እየተዋደቀ እንደሚገኝ የሚያጠያይቅ አይደለም። ከዘመነ ወያኔ ጀምሮ በዘርና በቋንቋ የተሸነሸነችው ሀገራችን፣ በአርባ ጉጉና በደኖ የተጀመረው አማራው ላይ ያነጣጠረው የዘር ፍጅት አድማሱን አስፍቶ የአማራ ዘር በአለበት መላ ኢትዮጵያ እየተፈናቀለ፣ እየተሰደደ፣ እየታሠረ፣ እየተራበና እየተገደለ ዛሬ እደረስንበት የሀገር ውድቀት ገደል አፋፍ ላይ እንገኛለን። ከዚህ አስከፊ ውድቀት ሀገራችንን ለማዳን በአማራው ፋኖ የሚካሄደው ፍልሚያ ተጠናክሮ ወደ ሕዝባዊ አመጽ በማሸጋገር ዘረኝነትን ለአንዴም ለመጨረሻም ለመቅበር በፍጹም ጽናትና ቆራጥነት የተነሱ ወገኖቻችንን ማየትና ማገዝ አግባብነት አለው እንላለን።

ኢትዮጵያን በማጥላላት ሲገዛ የኖረው የወያኔ/ህወሓት አገዛዝ ዘመኑ ሲያበቃ ተተኪ ሀገር አፍራሽ፣ ሕዝብ ገዳይ፣ አራጅና ጨካኝ፣ አፋኝና ዘራፊ፣ የመንግሥት ወንበዴ፣ የወንበዴ መንግሥት ላይ ወድቃለች። በኢኮኖሚው ሀገር ከማድቀቅ አልፎ ሕዝብን እያስራበና እየዘረፈ ሲጓዝ፣ በማህበራዊ ሕይወት በባህላችን ከቶም አፋችንን እንኳን ሞልተን የማንጠራውን የተመሳሳይ ፆታ ወስባዊ ግንኙነት እያራባና ትውልድ እየበረዘ፣ በፖለቲካው "ለኦሮሚያ የሆነች ሀገር እገነባለሁ" እያለ ሀገር አፍራሽ፣ ሃይማኖት በራዥ ለመስማትና ለማየት የሚዘገንን ዘመን ላይ ደርሰናል።

ይህ የዘር ማጥፋት ጉዞ ሀገር መጉዳቱ ቢታወቅም ግን ተወደደም ተጠላም ሊቀጥል አይችልም። ያበቃልም። ለዚህም ነው አማራውና ፋኖ በጋራ አማራውን ብቻ ሳይሆን ሀገር ለማዳን እየተፋለሙ ያሉት። የአማራው መዳረሻ ኢትዮጵያ ናትና ሉዓላዊነቷን የጠበቀች የሁሉም ዜጎቿ የሆነች ኢትዮጵያ፣ የእምነት ቤተ ክርስቲያንና መስጊዶቿን የጠበቀችና ያከበረች፣ የሰው ልጅ የዜግነት መብት የተከበረባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ አማራው ቀን ተሌት ሲዋደቅ ሌላ ቢቀር በሚቻለው ሁሉ ማገዝና ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ነው እንላለን።

***ዛሬ ከሁሉም በላይ ቅድሚያ የምንሰጠው የኢትዮጵያችን መኖር ነውና ሀገር እያፈረሰ ያለውን የብልጽግና/ኦሮሙማ አገዛዝ ከተካዩ የወያኔ/ህወሓት ቡድንና ከመጠለያቸው የዘረኝነት ቅርቃር ኢትዮጵያችንን ለማላቀቅ የአማራውን እንቅስቃሴ በአማራ ሕዝባዊ ግንባር በኩል በማገዝ ሀገራዊ ግዴታችንን መወጣት አስፈላጊ መሆኑን እናሰምርበታለን።***

በውጭ ኃይሎች ተባባሪነትና አጋዥነት ሀገራችን ላይ ያንዣበበውን መከራ ልንወጣ የምንችለው እራሳችን ብቻችንን መሆኑን ከታሪካችን ከተማርን አያቅተንምና ያንቀላፋን እንንቃ። በዘመኑ ስልጣኔ በታንክና በአውሮፕላን፣ በሀገር በቀል ባንዳ ታግዞ የመጣን ወራሪ ኃይል በጋሻና ጎራዴ የመከተ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ለሀገራችን ለአፍሪካና ለጥቁር ሕዝቦች ነጻ መውጣት ፈር ቀዳጅ ነንና ያኔም የእኛው ጀግኖች ናቸው ሀገርን ያስረከቡን። አሁንም ከአፍ እስከ አፍንጫዬ ታጥቄአለሁ በሚል በእብሪት የተወጠረውን የብልጽግና ዘረኛ አገዛዝ ለመቅበር ከጦርና መሳሪያ በላይ አስፈላጊው ወኔና የዓላማ ጽናት ነውና ለዚህ ደግሞ ዛሬም ቆራጥና አኩሪ ልጆች እንዳላት እየታየ ነውና ሀገርን ለትውልድ ለማስረከብ በምታደርጉት ተጋድሎ የችሎታችንን ያህል ድጋፋችን አይለያችሁም፣ ***በአማራው ተጋድሎ ድሉ የኢትዮጵያችን ይሆናል*** ስንል አቋማችንን እናሳውቃለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!
ሰኔ 26 ቀን 2015 ዓ.ም. (July 3, 2023)
"ኢትዮጵያችን" ሀገር ወዳድ ወገኖች

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org, www.ethiopiachen.com